Shelter Cluster Approach: Gedeo and West Guji

Version 4: 25 November, 2018

የመጠለያ ክላስተር አቀራረብ፡- ጌድዮና ምዕራብ ጉጂ

ቅጂ 4፡ ህዳር 16 ቀን 2011 ዓ.ም.

የሚከተለው ሰነድ በጊዲዮና በምዕራብ ጉጂ የመጠለያና የምግብ እርዳታ አቅርቦት ላይ የተሰማሩ የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶችን ግቦችና የአሠራር ዘዴዎች ይገልጻል። አለማቀፍ የሰብአዊ የሰብአዊ እርዳታ መርሆዎችንና አለማቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ሕግን መነሻ ያደረገ ነው።

ሰነዱ በዋነኝት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ብሔራዊ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ግብ አጣጣል አገር አቀፍ መመሪያ ምዕራፍ 13፣ የግብ አጣጣል ዘዴዎችና ስልቶች ላይ የተመሠረተ ነው። በተለይ የግብ አጣጣል መሠረታዊ መርሆዎች የአብአዊ እርዳታ ደርጅቶችን[1i] ያሳተፈ፣ በፍላጎት ላይ የተመሠረተና እርዳታው ከሁሉ የበለጠ ተጋላጭ ለሆኑትና አስቸኳይ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ቀዳሚ ትኩረት መስጠት እንዳለበት በአጽንኦት ይገልጻል።

> *“በጥሩ ሁኔታ የተጣለ የሰብአዊ እርዳታ በአደጋ የተጎዱትን ሰዎች ሕይወትና አኗኗር መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሰዎች በተቻለ ፍጥነት ከአደጋው ድነው ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ይታደጋል፣ የወደፊት የእርዳታ ጥገኝነትን ይቀንሳል።”* - አቶ ምትኩ ካሣ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ

**የመጠለያ ክላስተር ግብ ለኢትዮጵያ መንግሥት፡-**

ሀ) ለተፈናቃዮች (አይዲፒ) እና ለስደት ተመላሾች ሰዎችን አትጉዳ ለተመላሾች ጥበቃ አድርግ በሚል መርህ የሚመራ የህይወት አድን እርዳታ ለማቅረብ፤

ለ) መፈናቀል (አንድ ጊዜም ሆነ በተከታታይ የሚከሰት) የሚያስከትለውን ጉዳት ከመጠለያ አይነትና በሚስማማ የእርዳታ አቅርቦት ለመቀነስና የሚመለከታቸው ሰዎች ሃሳብ ለማክበር፤

ሐ) የኤችኤልፒ ጥናት እንደሚያሳየው በግለሰብ ደረጃ ተፈናቃይ ቤተሰቦች በግል በፈቃደኝነት ወደቀዬአቸው ሲመለሱ ቤታቸው ተከብሮ ደህንነታቸው ተጠብቆ በዘላቂነትና ተመልሰው የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖሩ፤ ነዋሪዎች ከማንኛውም ሌላ ተጨመሪ ስጋት ነጻ ሆነው ቤታቸውን ማደስና በአዲስ መልክ ለመገንባት የሚችልበትን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

**የተጠቃሚዎች ምዝገባ፣ ልየታና ማጣሪያ**

---

[1] በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሰብአዊ እርዳታ አጋር ድርጅቶች ሠራተኞች በእርዳታ ሰጪው አካል መካተት አለባቸው “የብሔራዊ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ግብ አጣጣል አገር አቀፍ መመሪያ” በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፣ 5፣ 2011 (ገጽ 55)

“በቤተሰብ አባላት ምዝገባ ከቁጥር አሳንሶ ማስመዝገብ ተቀባይነት ሌለው በመሆኑ መታረም አለበት። የተጠቃሚዎችን ልየታ ራሱን ከማምታታት ከተጨማሪ ከምዝገባ ዝርዝሩ ማን ምን እንዳገኘ የሚያሳይ ትክክለኛ ሪኮርድ ለማግኘት ከሞላ ጎደል የማያስችል ያደርገዋል”[2]

አሳንሶ ማስመዝገብና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በቅደም ተከተል ከማስቀመጥ የተያያዘ ተግዳሮት መታየቱ ተገልጾአል፡፤ ከታች የቀረበው መመሪያ ለሰብአዊ እርዳታ ኤጀንሲዎች የመንግሥትን የሰብአዊ እርዳታ ምላሽ ለመደገፍ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ቁልፍ ሥራ የሆነውን በገለልተኛ አካል የሚካሄድ ምዝገባ አስፈላጊነት በአጽኦት ይገልጻል።

ቅድሚያ ከሁሉም ለስጋት ተጋላጭ ለሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች መሰጠት አለበት፣ የተጠቃሚዎች ልየታ ፍላጎትን መነሻ ያደረገ መሆን አለበት (ገለልተኝነትና ግልጽነት ያለበት የተጋላጭነትና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የፍላጎት ጥናት)። በኢትዮጵያ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ተረጂዎች ልየታ ተሳትፎ ያላቸው ሁሉም ሁሉም ተዋንያንና ድርጅቶች እነዚህን ደረጃዎች ለማሟላት ጥረት ማድረግ አለባቸው።[3]

የተጠቃሚዎች ልየታ ሥራ አግባብ ያላቸው የወረዳ አስተዳደር፣ ዲአርኤምኦ፣ ሌሎች አግባብ ያላቸው የወረዳ ጽ/ቤቶች፣ የተጠቃሚ ቀበሌዎች ተጠሪዎች፣ (የክላስተር ስምምነት በተደረገባቸው መሠረት)፣ አግባብ ያላቸውን የክላስተር አስተባባሪዎች (ብዙውን ጊዜ ኤስኤምኤስና መከላከያ እንዲሁም መጠለያ)፣ አጋሮች (መያዶች ወይም የተመድ ኤጀንሲ)፣ የተጎጂው ማህበረሰብና አባላትና ምናልባትም በወረዳው የሚንቀሳቀሱ ሌሎች ኤጀንሲዎች ተሳታፊ በሚሆኑበት ስብሰባ ይጀመራል። ማህበረሰቦች በመጨረሻ ደረጃ የተጠቃሚዎች ልየታ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውሣኔ በማሳለፍ የሚጫወቱት ቁልፍ ሚና አላቸው (በእርዳታ ተጠቃሚ ቤተሰቦችንና ግለሰቦች ምዝገባ)።[4] ይህ ስበሰባ የማንኛውም ምልምል ተጠቃሚ ዝርዝር ምዝገባ ከመካሄዱ በፊት እንዲሁም ቁሳቁስ ወደ ወረዳ ወይም ቀበሌ የማጓጓዝ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት መካሄድ አለበት። የመጀመሪያው ሰብሰባ የምዝገባ ኮሚቴ ከማቋቋም በተያያዘ ለሚከተሉት ሶስት ቁልፍ ነጥቦች ምላሽ መስጠት አለበት።

1. የሥርጭቱን አላማ ማብራራት፡- ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑና ለምን እንደሆነ ግልጽ መሆን አለባቸው (ዝርዝር የተጋላጭነትና ሁኔታና የመጠለያ ችግር ክብደት የተጠቃሚዎች ልየታ መመሪያ ከታች ቀርቧል) ። እንዳስፈላጊነቱ ሀገራዊ የሰብዓዊ እርዳታ ቡድን በተወሰደው የመደበኛ የኦፕሬሽን መመሪያ፣ በለጋሾች ደንብና የሰብአዊ እርዳታ መርሆዎች ላይ ማብራሪያ መስጠት ይቻላል። ክርክር ከተነሳ የክላስተር አስተባባሪው (እና ኦሲኤችኤ) እገዛ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፤

[2] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 61

[3] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 61

[4] “የብሔራዊ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ግብ አጣጣል አገር አቀፍ መመሪያ” በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፣ 5፣ 2011 (ገጽ 18)

2. በወረዳው ውስጥ ተጠቃሚዎች የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች መለየትና ስምምነት ላይ መድረስ። እነዚህ የተወሰኑ የጋራ አገልግሎት ማዕከላት፣ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ብዙ ሰዎች የሚገኙባቸው ቀበሌዎች፣ የተወሰኑ መንደሮች፣ ጎጦች ወይም ተጎጂ ማህበሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። የመጠለያና የኤንኤፍአይ ክላስተር በዞን ደረጃ ከሁሉ ለከፋ ችግር የተዳጉትን ተረጂዎች ዝርዝር ወቅታዊ ለማድረግ ከከኦሲኤችኤ ጋር የሚሠራ ሲሆን መጀመሪያ እነርሱን ማማከር ያስፈልጋል፣ የቀበሌ ተጠሪዎች፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና በወረዳው የሚንቀሳቀሱ ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ መስጠት ይችላሉ። በዚህ ስብሰባ የቀበሌ ተጠሪዎች በእያንዳንዱ ታሳቢ የተጠቃሚዎች አካባቢ የምልምል ተጠቃሚዎችን ብዛት ሊጠቁሙ ይችላሉ- የተፈናቃዮችን አሃዝ ጨምሮ እንዲገልጹ መጠየቅ ሊያስፈልግ ይችላል። ስብሰባው ቀዳሚ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን በቅደም ተከተል ማስቀመጥና የተወሰኑ ተጠቃሚዎች ምዝገባ የሚካሄድባቸውን አካባቢዎች መምረጥ አለበት።

3. በመጨረሻም ስብሰባው በተጠቃሚዎች ምዝገባ ሥራው ተሳታፊ በሆኑት የኮሚቴ አባላት ቁጥር ላይ ስምምነት መድረስና በእያንዳንዱ ሥፍራ የሚካሄደውን የምዝገባ ዕቅድ/ መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለበት።

ኮሚቴው የሚቋቋመው ለተጠቃሚዎች ምዝገባ ከሆነ አግባብ ያላቸው ወገኖች በድጋፍ ሰጪ ኤጀንሲ እየታገዙ የምዝገባ ሥራውን በቡድን መስራት አለባቸው። ይህ በማጣሪያና ማረጋገጫ ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የተለያዩ ተግዳሮቶች በመቀነስ ለሥርጭቱ በትክክል ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዕቃዎች ለመስጠት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

በተረጂዎች ምዝገባ የእርዳታ ኤጀንሲዎች ተሳትፎ በመንግሥት ካልተፈቀደ ምላሽ ሰጪው ኤጀንሲ ጉዳዩን ለመጠለያ ክላስተር አስተባባሪው፣ ለኦሲኤችኤ እና በአዲስ አበባ ለሚገኘው የካንትሪ ት/ቤት ማሳወቅ አለበት።

## የተወሰኑ ችግሮች (ፒኤስኤን) እና የከፋ የመጠለያ ችግር ደረጃ

የመጠለያ ችግር ያለባቸው ሰዎች ብዛትና ምግብ ነክ ላልሆኑ ቁሳቁሶች ካለው ክምችት ይበልጣል። ኤጀንሲዎች አቀራረባቸውን በተወሰነ የተፈናቃዮች ፍላጎት ላይ ያተኮረ መደበኛ የተጠቃሚ ልየታ በመጠቀም በሚያቀርቡት እርዳታ ወጥነት ያለው የተቀናጀ አቀራረብ ለመከተል ተስማምተዋል። በተወሰኑ ጉዳዮች ባልተፈናቀለው የአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ የሚታዩ አንገብጋቢ ፍላጎቶች ካሉ የእርዳታ ኤጀንሲዎች ይህንኑ መስፈርት በመከተል ለዚያ ቀበሌ ከተዘጋጀው ጠቅላላ የእርዳታ አቅርቦት ብዛት ከአስር በመቶ የማይበልጥ እርዳታ የማቅረብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ቤተሰቦችና ሌሎች ሰዎች በአሁኑ ቀውስ ከሁሉም በላይ ተጎጂ ናቸው ተብሎ ይገመታል፤ በመሆኑም ለሰብአዊ እርዳታ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች መሆን አለባቸው። ከፍላጎት ውጭ በተጠቃሚዎች መረጣ ሂደት ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛንውም ሌላ ሁኔታ (የቤተሰብ ዝምድና፣ ጓደኝነት፣ ጠብ ወይም ጥላቻ ጨምሮ) ታሳቢ ያደረገ አሠራር መፈቀድ የለበትም። እርዳታ ለእያንዳንዱ

ተረጂ እኩል መከፋፈል አለበት፤ ሆኖም በሰዎች የተለያየ የፍላጎት ደረጃ መሠረት በፍትሃዊ መንገድ (በትክክል) መከፋፈል አለበት።[5]

1. የተለዩ/ ለጉዳት የተጋለጡ ህጻናት
2. ለጉዳት ተጋላጭ ሴቶች
3. ለጉዳት ተጋላጭ አረጋውያን
4. ነፍሰጡር ሴቶች
5. በአንድ አባወራ/ እማወራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች
6. አካል ጉዳተኞች/ ማየት የተሳናቸው/ ከባድ የጤና ችግር ያለባቸው
7. ልዩ የሕግ ጥበቃና ከለላ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች
8. በድህነት ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ለጉዳት የተጋለጡ ሰዎች (በማህበረሰቡ የተለዩ)

## ስጋት ቅነሳ

በተወሰነ ቤተሰብ እርዳታ ለመቀበል የተፈቀደለት ሰው ከቤተሰበ አባላት በእድሜ ትንሽና፣ ብቁ ሊሆን እንደሚችል ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ግልጽ መደረግ አለበት። ይህም እንደ ሁሉም ደረጃዎች በቅድሚያ ማብራሪያና በተጨባጭ የሚታይ ማረጋገጫ ይጠይቃል።

ፒኤስኤን ራሳቸውን ችለው እርዳታ የመቀበል ችሎታ የሌላቸው ሆነው በሚገኙበት ጊዜ የሎጀስቲክስ ደጋፍ ማግኘት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፤ በዚህ ሁኔታ ረዘም ያለ ርቀት ከሆነ፣ የተቀበሉት ዕቃ ከባድ ከሆነ ወይም ከጥበቃ አንጻር ያለባቸው ስጋት ከፍተኛ ኤጀንሲዎች ይህን ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

በሁሉም ደረጃ የደህንት ጥንቃቄ ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ አግባብ ካላቸው ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ከተግባራቸው፣ ከኃላፊነታቸው፣ ከዕቅድ ዝግጅትና በእርዳታ አቅርቦትና በጥበቃ ተሳትፎ ያላቸው ተዋንያን ግዴታቸውን በትጋት ከመፈጸም አንጻር ግልጽ ግንኙነትና ስምምነት ማድረግ ይጠይቃል።

**የሚከተሉት ስጋቶች የሥራ እንቅስቃሴዎችን እገዳ ሊያስከትሉ ምክንያቶች በመሆናቸው በቅድሚያ ሥራ እንደገና ከመጀመሩ በፊት ክለሳ ማድረግ የሚጠይቁ ናቸው።-** የሚከተለው ከሰብአዊ እርዳታ ሰጪው የአገር ቡድን የተወሰደ በመጠለያ ክላስተር ኤጀንሲዎች ስምምነት የተደረገበትን መመሪያ ይጨምራል፡-

---

[5] “የብሔራዊ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ግብ አጣጣል አገር አቀፍ መመሪያ” በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፣ 5፣ 2011 (ገጽ 62)

ሀ) የተጠቃሚዎች ልየታ (እና ማረጋገጫ)፡- ማንኛውም የእርዳታ ሥርጭት ከመካሄዱ በፊት አጋሮች የተስማሙባቸው ተጠቃሚዎች ከተስማሙባቸው ተጠቃሚዎች መካከል የከፋ ችግር ያለባቸው/ አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ከዚህ የተለየ ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ የታቀደው (የተጠየቀው) የእርዳታ ሥርጭት ወዲያውኑ ቆሞ ጉዳዩ ለተጨማሪ ክለሳና ለውሣኔ የድንገተኛ ኦፕሬሽን ማዕከል አስተባባሪዎች፣ ለክላስተር አስተባባሪውና ለኦሲኤችኤ መገለጽ አለበት።

ለ) የስጋት ምዘና፡- ማንኛውም የእርዳታ ሥርጭት/ እንቅስቃሴ ከመካሄዱ በፊት አጋሮች የሥራ እንቅስቃሴው ከጥበቃ የተያያዙ ስጋቶችን የሚያያባብስ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣ ለተጠቃሚ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች የሚያስገኘውን ጠቀሜታ፣ በተጎጂ ማህበረሰቦች፣ በሰብአዊ እርዳታ ሰጪ ኤጀንሲዎችና በመንግሥት እና/ወይም በተጨማሪ የፕሮግራም ሥራዎች አማካኝነት ሊቀነሱ የሚችሉ አዳዲስ አዳዲስ ስጋቶች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን ተሰቢ ያደረገ ስጋት ትንተና ማካሄድ አለባቸው። ይህ በኤችኤች - ከተወሰኑ የእርዳታ፣ ለምሳሌ መልሶ ግንባታ/ ጥገና ከመሣሠሉ ሥራዎች አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ተግባር ነው።

ሐ) ለተጎጂው ሕዝብ ያለበት ተጠያቂነት፡- ተጎጂ ማህበረሰቦችን በተወሰኑ የምላሽ ሥራዎች ዲዛይን ቀረጻ ሂደት ተሳታፊ ማድረግን- ተጠቃሚ ማህበረሰቦች ከጥበቃ የተያያዙ የራሳቸውን ስጋቶች በመለየት ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ መጋበዛቸውን ማረጋገጥ ይጨምራል። የፕሮግራሙን ግቦች ለሁሉም የማህበረሰብ አባላት ማብራራት- ተጠቃሚ ያልሆኑትን ጨምሮ።

መ) ከመንግሥት (ወይም "በተጠየቀው" የሰብአዊ እርዳታ መርሆዎች ከተቀመጡት ነጥቦች) የሚነሱ ሞጋች ጥያቄዎች መስተናገድ የለባቸውም።

ሠ) አጋሮች ለአውቶቡስ/ ለጭነት መኪና ተሳፋሪዎች መጠለያ/ ኤንኤፍአይ አያቀርቡም (የማትጊያ ምላሽን ለማስቀረት)

---

[i] በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሰብአዊ እርዳታ አጋር ድርጅቶች ሠራተኞች በእርዳታ ሰጪው አካል መካተት አለባቸው "የብሔራዊ የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ግብ አጣጣል አገር አቀፍ መመሪያ" በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዳሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርና የምግብ ዋስትና ዘርፍ፣ 5፣ 2011 (ገጽ 55)

2. ዝኒ ከማሁ (ገጽ 61